# ደምብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**

*ተዛማጅ የመረጃ ምንጭ:-* ACA, ACA-RA, ACG, ACG-RB, BLB
*ሀላፊነት ያለው ቢሮ:-* ዋና የስራ ሂደት ሀላፊ፤ የሰው ሀብትና ልማት ቢሮ

## የሥራ ቅጥር፣ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች፣ እና አክቲቪቲዎችን በሚመለከት አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ግለሰቦች በተገቢ ሁኔታ ስለማመቻቸት እና ማሻሻያዎች

### I. ዓላማ

አካል ጉዳተኛ ከሆኑ የማህበረሰብ አባላት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች እና ከስራ አመልካቾች የሚቀርቡ የማመቻቸት/አኮሞዴሽን ጥያቄዎችን የአካል ጉዳት ያለባቸው አሜሪካውያን ህግ 2008 የማሻሻያ ህግ ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ ለማስተናገድ/ለማካሄድ የአሰራር ቅደም ተከተሎችን ለማስቀመጥ

### II. ርዕሰ ጉዳይ

A. ይሄ ደንብ ተፈጻሚነት የሚኖረው ብቁ የሆኑ የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው የማህበረሰብ አባላት በማንኛውም የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አገልግሎት ላይ ለሚኖራቸው ተሳትፎ፤ የ MCPS የስራ ማመልከቻ ሂደት፤ የሰራተኞች ቅጥር፣ እድገት ወይም ስንብት፤ የሰራተኛ ካሳ ክፍያ፤ እና የስራ ስልጠና እና ሌሎች ተግባሮች፣ ሁኔታዎች እና ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ነው። የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ብቁ ተማሪዎች አሰራር ሂደቶች ደንብ ACG-RB ላይ ተደንግገዋል፣ 1973 የማገገሚያ ህግ ሰክሽን 504 ስር ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ማመቻቸት እና ማሻሻያዎች።

B. የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው አሜሪካውያን ህግ 2008 የማሻሻያ ህግ (ADAAA) ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ሲሆን በሥራ ቅጥር፣ በስቴት እና በአካባቢ የመንግስት አገልግሎቶች እና በቴሌኮምዩኒኬሽን መስኮች ውስጥ የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ብቁ ግለሰቦች ጥበቃ የሚሰጥ ነው። ይሄ ደንብ መተርጎም ያለበት ADAAA ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ እና ከመተግበሪያ ደንቦቹ ጋር ነው።

C. የአካል ጉዳተኛ ግለሰብ ማለት—

1. አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳተኝነት/ስንክልና ያለበ(ባ)ት ግለሰብ፣ ጉዳተኝነቱ የግለሰብን አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና የህይወት ክንውኖችን በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ፣

2. የዚህ አይነት ጉዳተኝነት/ስንክልና መኖሩ የተመዘገበ ግለሰብ፣ ወይም

3. የዚህ አይነት ጉዳተኝነት/ስንክልና መኖሩ የሚታወቅ ግለሰብ።

    a) አንድ ግለሰብ የዚህ አይነት ጉዳተኝነት/ስንክልና እንዳለበ(ባ)ት መስፈርቱን የሚያሟላው/የምታሟላው ግለሰቡ/ቧ ተጨባጭ ወይም ይሆናል ተብሎ በመገመት አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳተኝነት የተነሳ መገለል እንደደረሰበ(ባ)ት ካረጋገጠ/ች ነው። ይሄ ጊዜያዊ ወይም ዝቅተኛ ደረጃ የአካል ጉዳተኝነትን አያካትትም። ጊዜያዊ

ጉዳተኝነት/ስንክልና ማለት ቆይታው ለስድስት ወራት ወይም ከዚያ በታች የሆነ ወይም እንደሚሆን የሚጠበቅ የአካል ጉዳተኝነት/ስንክልና ነው።

b) የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ግለሰብ ትርጓሜ ለማያ(ታ)ሟላ ግለሰብ የአካል ጉዳት እንዳለበ(ባ)ት በማሰብ ብቻ ፖሊሲዎችን፣ ተግብራትን፣ እና የአሰራር ሂደቶችን ማመቻቸት ወይም ማሻሻያዎችን ማድረግ አይገባም።

D. የሥራ ቅጥር ፖሊሲዎችን፣ ደንቦችን እና አሰራሮችን የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ግለሰቦችን መብቶች በጠበቀ/ባከበረ መንገድ ማካሄድ የአስተዳደር እና የቁጥጥር ሰራተኞች ሀላፊነት ነው።

III. **ትርጉም**

A. ተጨማሪ ድጋፎች እና አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

1. በድምፅ የቀረቡ ነገሮችን መስማት ለተሳናቸው ግለሰቦች ተደራሽ ለማድረግ ብቃት ያላቸው አስተርጓሚዎች ወይም ሌላ ውጤታማ መንገዶችን ማዘጋጀት።

2. በእይታ/በምስል የቀረቡ ነገሮችን ማየት ለተሳናቸው ግለሰቦች ተደራሽ ለማድረግ ብቃት ባላቸው አንባቢዎች በድምፅ የተቀዱ ፅሁፎችን፣ ወይም ሌላ ውጤታማ መንገዶችን ማዘጋጀት።

3. መገልገያ ወይም መሳሪያዎችን ማግኘት ወይም ማሻሻያ።

4. ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች እና ተግባራት።

B. ቀጥተኛ ስጋት ማለት ተገቢ ዝግጅት በማድረግ ማስወገድ ወይም መቀነስ የማይቻልና በሌሎች ጤና ወይም ደህንነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ከፍተኛ ስጋት/አደጋ ማለት ነው።

C. MCPS ይሄን በመጠቀም እርምጃ በሚወስድበት ጊዜ፥ እነዚህ ስያሜዎች፣ የአካል ጉዳተኝነት እና ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ብቁ ግለሰብ አሁን ላይ ህገ ወጥ ዕፆችን እየተጠቀሙ ያሉትን ግለሰቦች አያካትትም።

D. መሰረታዊ ተግባራት የሚባሉት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በወሰነው መሰረት የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ግለሰብ የያዘ(ች)ው ወይም ለመያዝ የሚፈልገው/የምትፈልገው የስራ መደቡ መሰረታዊ የስራ ሀላፊነቶች ናቸው። የዚህ አተገባበር የስራ መደቡን ተጓዳኝ ስራዎች/ተግባራት አያካትትም።

E. የግንኙነት ሂደት ማለት፡- በስራ ቀጣሪ እና ተገቢ ማመቻቸት ወይም ማሻሻያ በጠየቀ(ች) የአካል ጉዳተኛ ግለሰብ መካከል የሚደረግ መረጃ-የመሰብሰብ ግንኙነት ነው፣ ሊያካትት የሚችለውም የሰራተኛ ስራን መሰረታዊ ተግባራት ለመተንተን፣ በግለሰቡ(ቧ) የአካል ጉዳተኝነት የተነሳ የሚከሰቱ ከስራ-ባህርይ ጋር ተዛማጅ የሆኑ እክሎችን ለመወሰን፣ እና ሰራተኛው(ዋ) መሰረታዊ ተግባሮችን ለማከናወን የሚያስችሉ ተገቢነት ያለው ማመቻቸትን ለመለየት ከሰራተኛው(ዋ) ተቆጣጣሪ እና ከሰራተኛው(ዋ) የጤና አገልግሎት ሰጪ ባለሙያ ጠቃሚ መረጃ መሰብሰብ ነው።

F. ዝቅተኛ የእይታ መሳሪያዎች ማለት፡- የሚታይ ምስልን የሚያጎሉ፣ የሚያሻሽሉ፣ ወይም ደግሞ የአንድን ነገር መጠን የሚጨምሩ መሳሪያዎች ማለት ነው።

G. ዓብይ የህይወት ተግባራት እንቅስቃሴዎች የሚያካትቱት በእነዚህ ብቻ የተገደቡ ባይሆኑም፡- ራስን መንከባከብ፣ በአካል የሚሰሩ ስራዎችን ማከናወን፣ ማየት፣ ማዳመጥ፣ መተኛት፣ መራመድ፣ መቆም፣

መሸከም፣ መታጠፍ/ዝቅ ማለት፣ መናገር፣ መተንፈስ፣ መማር፣ ማንበብ፣ ማተኮር፣ ማሰብ፣ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ እና መስራትን የመሳሰሉ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን የሚጠይቁ ተግባራት ናቸው። በተጨማሪም ዓብይ የህይወት ተግባር የሚያካትተው ዋነኛ የሰውነት ተግባር መስራትን ነው፣ ይሄውም በዚህ ብቻ ባይወሰንም የሚያካትተው፦ የሰውነት በሽታ የመቋቋም ስርዓት (immune system) ስራዎች፣ ጤናማ/መደበኛ የሰውነት ህዋስ (cell) እድገት፣ እና የሰውነት ምግብ የመፍጨት፣ የመፀዳጃ፣ የሽንት፣ የአዕምሯዊ፣ የአንጎል፣ የአተነፋፈስ፣ የደም ዝውውር፣ የኢንዶክሪን ሆርሞን በደም ዝውውር (endocrine) እና የመራቢያ አካላት ስራዎችን ነው። የአካል ጉዳተኛ ለመባል፤ አንድን ዋና የህይወት እንቅስቃሴ ተግባር በከፍተኛ ደረጃ የሚገድብ ጉዳተኝነት/ስንክልና ሌላ ዋና የህይወት ተግባሮችን እንቅስቃሴ መገደብ አይኖርበትም።

H. መቆጣጠሪያ እርምጃዎች በዚህ ብቻ ባይወሰኑም የሚያካትቱት፦ መድሀኒት፣ የህክምና አቅርቦቶች፤ መሳሪያዎች ወይም መጠቀሚያዎች፤ የዝቅተኛ-ዕይታ መሳሪያዎች (እነዚህ መደበኛ የአይን መነፅሮችን ወይም የዕይታ ሌንሶችን (contact lenses) አያካትቱም)፤ ሰው-ሰራሽ የሰውነት አካላት የሚያካትቱት፦ መገጣጠሚያዎች እና መሳሪያዎችን፣ ለመስማት የሚረዱ መሣሪያዎችን እና ድምፅ ከጆሮ ወደ አዕምሮ ማስተላለፊያ (cochlear) በሰውነት ውስጥ የሚገቡ/የሚቀመጡ ወይም ሌላ በሰውነት ውስጥ የሚቀበሩ/የሚቀመጡ የማዳመጫ መሳሪያዎች፣ የመንቀሳቀሻ መሳሪያዎች፣ ወይም የኦክስጅን ክህምና መሳሪያዎች ወይም አቅርቦቶችን ነው። ደጋፊ ቴክኖሎጂን መጠቀም፤ በተገቢ ሁኔታ ማመቻቸት ወይም ተጨማሪ ድጋፎች እና አገልግሎቶች፤ ወይም በመሠልጠን የተገኘ ባህሪ ወይም የመላመድ አዕምሯዊ ማስተካከያዎች ናቸው።

I. አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳቶች/ስንክልና ማለት የሚከተለው ነው፦

1. ማንኛውም አካላዊ መዛባት ወይም ህመም፣ የውበት መበላሸት፣ ወይም የአካል መጉደል ሆነው ከሚከተሉት አንድ ወይም ከዚያ በላይ በሚሆኑ የሰውነት ክፍል ስርዓቶች ላይ ተፅዕኖዎችን የሚፈጥሩ፦ አዕምሯዊ/ኑዩሮሎጂካል፣ የጡንቻ-የአጥንት፣ ልዩ የስሜት ህዋሳት፣ የመተንፈሻ (የንግግር አካላትን ጨምሮ)፣ የልብ እና የደም ዝውውር፣ የመራቢያ አካላት፣ የምግብ መፍጫ/አንጀት፣ የብልት-የሽንት (genito-urinary)፣ የደም (hemic) እና የደም ነጭ ሴሎች (lymphatic) መዘዋወሪያ፣ የቆዳ፣ እና የኢንዶክሪን ሆርሞን በደም ዝውውር (endocrine)፤ ወይም

2. ማንኛውም አዕምሯዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ መዛባት፣ የአስተሳሰብ/እውቀት ጉዳተኝነት፣ የተፈጥሯዊ አንጎል ህመም፣ የስሜት ወይም የአዕምሮ ህመም፣ እና ልዩ የመማር ጉዳተኝነቶች ናቸው።

J. የቃሉ ፍቺ፦ ዳይሬክተር/አስተዳደር ማለት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤት ዳይሬክተር ወይም ት/ቤት ያልሆነ የ MCPS የሥራ ክፍል ሀላፊ የሆነ/ች ግለሰብ ነው።

K. የፕሮግራም ተደራሽነት ማለት፦ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አገልግሎቶች፣ እንደ አጠቃላይ ሲታዩ፣ አካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ብቁ ግለሰቦች ቀድመው ተዘጋጅተው ተደራሽ የሚሆኑ እና ሊጠቀሟቸው የሚችሉት ማለት ነው።

L. የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ብቁ ግለሰብ ማለት የሚከተለው ነው፦

1. የሥራ ቅጥርን በሚመለከት፣ ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ግለሰብ ሆኖ/ና የዚህ አይነት ግለሰብ የያዘ(ች)ው ወይም የሚፈልገው/የምትፈልገው የስራ መደብ እንዲሟላ የሚጠይቀው ክህሎት፣ ትምህርት፣ እና ሌላ ከስራው ጋር-ተዛማጅ መስፈርቶችን ካሟላ(ች)፣ እና ተገቢ የሆነ ማመቻቸት ቢኖርም ባይኖርም፣ የስራ መደቡን መሰረታዊ ስራዎች ማከናወን የሚችል/የምትችል።

2. አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች እና ተግባራትን በሚመለከት፣ ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ግለሰብ ሆኖ/ና—በህጎች፣ በፖሊሲዎች ወይም አሰራሮች ላይ፤ የህንፃ፣ የግንኙነት ወይም የመጓጓዥ ተግዳሮቶች (አስቸጋሪ ሁኔታዎች) መወገድ ላይ፤ ወይም ተጨማሪ ድጋፎች እና አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ አግባብ የሆነ ማመቻቸት ቢኖርም ባይኖርም—በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለመውሰድ ወይም በፕሮግራሞች ወይም ተግባራት ላይ ለመሳተፍ መሰረታዊ የብቁነት መስፈርቶችን የሚያሟላ/የምታሟላ።

M. የሥራ ቅጥርን በሚመለከት ተገቢ የሆነ ማመቻቸት ማለት የሚከተለው ነው፡-

1. የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ብቁ የሆነ(ች) የስራ አመልካች ግለሰብ ለሚፈልገው/ለምትፈልገው የስራ ዘርፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚያስችሉ የስራ ማመልከቻ ሂደት ላይ ለማመቻቸት ማሻሻያዎችን ማድረግ።

2. የስራ አካባቢን ወይም የሚፈለገው የስራ ዘርፍ በመደበኛነት የሚከናወንበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት እና ማሻሻል፣ብቁ የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ግለሰብ የስራ ዘርፉን መሰረታዊ ተግባራት ማከናወን ለማስቻል ነው።

3. የአካል ጉዳተኝነት ላለበ(ባ)ት የ MCPS ሰራተኛ በአግባቡ ማመቻቸት እና ማሻሻያዎችን ማድረግ ማለት የስራ ቅጥርን እና ጥቅማ ጥቅሞችን የአካል ጉዳተኝነት የሌለባቸው የ MCPS ሰራተኞች እንደሚያገኟቸው ተመሳሳይና በእኩልነት ማግኘት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

4. አግባብ ያልሆነ ማመቻቸት የማያካትተው ያልተገባ ልፋትን የሚያስከትል፣ የሚደረገው ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ የስራ ዘርፉን መሰረታዊ ተግባር የሚያስወግድ ወይም ምደባውን መለወጥ የሚያስፈልገው፣ ወይም የግለሰቡ(ቧ)ን ወይም የሌሎችን ጤና ወይም ደህንነት በቀጥታ ስጋት ላይ የሚጥል ሲሆን ነው።

N. አገልግሎቶችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ወይም ተግባራትን በሚመለከት አግባብነት ያላቸው ማሻሻያዎች ማለት የሚከተለው ነው፡-

1. በአካል ጉዳተኝነት ምክንያት ማግለልን ለማስወገድ የሚደረግ የፖሊሲ፣ የአሰራር ወይም የአካሄድ ምክንያታዊ ማሻሻያ መደረግ ያለበት ማስተካከያው ያልተገባ ልፋትን የማያስከትል ከሆነ፣ የአገልግሎቱን አሠራር ሁኔታ በመሰረታዊነት የማቀይር ከሆነ፣ ወይም የግለሰቡ(ቧ)ን ወይም የሌሎችን ጤና ወይም ደህንነት በቀጥታ ስጋት ላይ የማይጥል ከሆነ ብቻ ነው።

2. የአካል ጉዳተኝነት ላለበ(ባ)ት ብቃት ያለው/ያላት ግለሰብ የአገልግሎት አሰጣጥን ተደራሽ ማድረግ የሚያስፈልገው የአሰራር ስልቱ ያልተገባ ልፋትን የማያስከትል ከሆነ፣ የአገልግሎት አሰጣጡን ተፈጥሮ በመሰረታዊነት የማይቀይር ከሆነ፣ ወይም የግለሰቡ(ቧ)ን ወይም የሌሎችን ጤና ወይም ደህንነት በቀጥታ ስጋት ላይ የማይጥል ከሆነ ነው።

3. የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ብቁ ግለሰቦች ተጨማሪ የመገልገያ ድጋፎችን ማቅረብ የሚከናወነው እነዚህ ተጨማሪ የመገልገያ ድጋፎች የአገልግሎቱን ተፈጥሮአዊ ሁኔታ በመሰረታዊነት የማይቀይር ከሆነ ወይም፣ ያልተገባ የገንዘብ እና የአስተዳደር ጫና የማይፈጥር ከሆነ ነው።

O. ይሄ አገልግሎቶች የሚለው ስያሜ የሚያካትተው ማንኛውም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚቀርቡ አገልግሎቶችን፣ ፕሮግራሞችን እና ተግባራትን ነው።

P. በከፍተኛ ደረጃ የተገደበ ማለት የሚከተልው ነው፡-

1. በአጠቃላይ ማህበረሰቡ እንደሚያደርገው ከአብዛኛዎቹ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር ዓብይ የህይወት ተግባራትን የማከናወን ብቃት/ችሎታ በከፍተኛ ደረጃ የተገደበ እንደሆነ ነው።

2. በየጊዜው የሚነሳ እና ጋብ የሚል የህይወት ዋና እንቅስቃሴዎችን በከፍተኛ ደረጃ የሚገድብ ከሆነ ስንከልና ነው።

3. የአካል ጉዳተኝነት ዋነኛ የህይወት እንቅስቃሴ ተግባራትን በከፍተኛ ደረጃ የሚገድብ መሆኑን ለማረጋገጥ መደረግ ያለበት ነገሮችን ለማሻሻል የማስተካከያ እርምጃዎች የሚኖራቸውን ውጤት ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

4. አንድ ግለሰብ በአብይ የህይወት እንቅስቃሴ ተግባር ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተገድቧል/ተገድባለች ብሎ ለመወሰን የሚከተሉት ምክንያቶች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

   a) የአካል ጉዳተኝነቱ ተፈጥሮ እና መጥፎነት/ከባድነት፣

   b) የአካል ጉዳቱ የሚቆይበት ያህል ጊዜ ወይም ተገማች የሆነ የሚቆይበት ጊዜ፤ እና

   c) ቋሚ ወይም የረጅም ጊዜ ጉዳት/ተፅዕኖ፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት በሚያድርሰው ተፅዕኖ ምክንያት የሚመጣ ቋሚ ወይም የረጅም ጊዜ ጉዳት።

Q. ያልተገባ ልፋትን ለማቅለል ከአቅርቦት አንፃር ያለው ትርጓሜ ከፍተኛ ተግዳሮት/አስቸጋሪ ሁኔታ ወይም ወጪ ነው፣ ይሄ ግምት ውስጥ ሲገባ መታሰብ ያለበት—

1. አኮሞዴሽን የማመቻቸት ወይም ማሻሻያ የማድረግ ባህርይ/ሁኔታ እና አጠቃላይ ወጪ፤

2. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አጠቃላይ የገንዘብ አቅም/ባጀት፤

3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አጠቃላይ የሠራተኞች ብዛት መጠን፤

4. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መገልገያዎች ቁጥር፣ አይነት፣ እና የሚገኙበት ቦታ፤

5. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚካሄደው ስራ(ዎች) አይነት፣ ይኼውም፡- MCPS በአጠቃላይ ሲታይ ጉዳዩ የሚመለከተው ት/ቤት ወይም ክፍል ከሚገኝበት ቦታ ርቀት እና አስተዳደራዊ ወይም የገንዘብ ግንኙነት አንፃር፤ እና

6. አኮሞዴሽን ማመቻቸት ወይም ማሻሻያ በት/ቤቱ ወይም ክፍሉ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ፣ ይኼውም፡- ሌሎች ሰራተኞች ወይም ግለሰቦች በሚያከናውኑት አገልግሎት ውስጥ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ወይም ለመሳተፍ የሚኖራቸው ብቃት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ፣ እና ት/ቤቱ ወይም ክፍሉ ስራውን የማካሄድ ብቃቱ ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ነው።

## III. የአፈጻፀም ቅደም-ተከተል

A. ADAAA መርህ ላይ በመመርኮዝ MCPS ሀላፊነቶቹን ለመወጣት የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎችና የሚያደርጋቸውን ጥረቶች የሰው ሀይልና ልማት ቢሮ (OHRD) የማስተባበር ሀላፊነት አለበት። ADA አስተባባሪ የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ብቁ ግለሰቦች መብቶች ጋር የሚዛመዱ ጉዳዮችን መመሪያዎች ይሰጣል። ADA አስተባባሪ አኮሞዴሽን ማመቻቸትን በሚመለከት ጥያቄዎችን የሚቀበለው/የምትቀበለው ከታች ሰክሽን III.B በተቀመጠው መሰረት ነው።

B. ስለ አኮሞዴሽን ማመቻቸት እና ማሻሻያዎች ለ፦ ADAAA ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ

1. አኮሞዴሽን እንዲመቻች ወይም ማሻሻያ እንዲደረግ ማን መጠየቅ የሚችለው ማነው?

a) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ የሆነ(ች) የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ብቁ ግለሰብ መሰረታዊ የስራ ተግባራትን ለማከናወን ወይም ሌላ እኩል ጥቅሞችን ለማግኘት ተገቢ የሆነ አኮሞዴሽን/ማመቻቸት እንዲደረግ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች፣ ይሄውም MCPS ቅፅ 270-6 ላይ ትክክለኛውን ክፍል በመሙላት ነው፣ ስለ ADAAA አኮሞዴሽን ማመቻቸት/ማሻሻያ የሰራተኛ ጥያቄ።

b) ለስራ አመልካች የሆነ/ች የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ብቁ ግለሰብ በማመልከቻ ሂደት ላይ ተገቢነት ያለው አኮሞዴሽን እንዲመቻች ጥያቄ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች። ስለ አኮሞዴሽን ማመቻቸት ጥያቄ ለማቅረብ ለሰው ሀብት አስተዳደር ክፍል ኢሜይል staffing@mcpsmd.org ሊደረግ ይችላል።

c) የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ብቁ ግለሰብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ብቁ በሆኑበት አገልግሎት ላይ ለመሳተፍ የአኮሞዴሽን/ማሻሻያ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል/ትችላለች።

(1) ግለሰቡ(ቧ) ስለሚጠየቀው አኮሞዴሽን ማመቻቸት/ማሻሻያ ከተጠየቀበት ምክንያት ጋር የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አገልግሎትን/ዝግጅትን ስፖንሰር ያደረገውን አካል ማነጋገር ይችላል/ትችላለች።

(2) ማመልከቻው የቀረበለ(ላ)ት ዳይሬክተር ወይም ተቆጣጣሪ ADA አስተባባሪ ጋር በኢሜይል ADArequests@mcpsmd.org መነጋገር ይችላሉ።

C. የግንኙነት ሂደት

1. ለማመቻቸት ወይም ለማሻሻያ የሚቀርብ ጥያቄ የሚወሰነው ADA አስተባባሪ የግንኙነት ሂደት በመጠቀም የስቴት እና የፌደራል ህጎችን መስፈርቶች በአከበረ መንገድ ነው።

a) አመልካቹ(ቿ) ቅፅ 270-6 ካልሞላ(ች)፣ ADA አስተባባሪ በግንኙነት ሂደቱ መጀመሪያ ላይ ከጥያቄ አቅራቢው(ዋ) ጋር በመነጋገር ቅጹ መሞላቱን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች።

b) በግንኙነት ሂደቱ ውስጥ የጉዳዩ አጠቃላይ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ።

2. የአካል ጉዳተኝነት ያለበ(ባ)ት ግለሰብ ADAAA ስር ለአገልግሎቱ ብቁ ከሆነ/ች፣ ADA አስተባባሪ የሚከተለውን ያደርጋል/ታደርጋለች፦

a) ግለሰቡ/ቧ የስራ መደቡን መሰረታዊ ተግባራት/ስራዎች ማከናወን መቻሉ(ሏ)ን ወይም በአግባቡ በማመቻቸት ወይም ማሻሻያ ተደርጎ ወይም ሳይደረግ መሰረታዊ አገልግሎት ለመስጠት የብቁነት መስፈርቶችን ማሟላት መቻሉን/ሏን ይወስናል/ትወስናለች።

b) ለግለሰቡ(ቧ) አኮሞዴሽን የማመቻቸት ሁኔታ ስራ ቦታ ላይ የግለሰቡ(ቧ)ን ወይም የሌሎች ጤና እና ደህንነት ላይ ቀጥተኛ ስጋት እንደሚፈጥር/እንደማይፈጥር ይወስናል/ትወስናለች።

c) በራስ ላይ ወይም የሌሎች ጤና እና ደህንነት ላይ ቀጥተኛ ስጋት የሚፈጥር ከሆነ፣ ስጋቱ ተቀባይነት ወዳለው ደረጃ ማመቻቻ ወይም አኮሞዴሽኑን ማስወገድ ወይም መቀነስ የሚቻል እንደሆነ ወይም እንዳልሆነ ውሳኔ ይሰጣል። (ቀጥተኛ ስጋት የሚፈጥር/የምትፈጥር ግለሰብ በአኮሞዴሽን ማመቻቻ ወይም ማሻሻያ በማድረግ ስጋቱ ተቀባይነት ወዳለው ደረጃ መቀነስ ወይም መወገድ የማይችል ከሆነ ብቁ አይሆንም/አትሆንም።)

d) ከሰራተኛው(ዋ)፣ወይም ሥራ ለመቀጠር አመልካች ግለሰብ ጋር በመመካከር መሰረታዊ የስራ ክንውኖችን ማካሄድ ወይም በአገልግሎት ላይ መሳተፍ የሚያስችል አኮሞዴሽን ማመቻቸት ወይም ማሻሻያ መለየት ወይም ለይቶ መወሰን።

e) የተጠየቀው ማመቻቻ ወይም ማሻሻያ ያልተገባ ልፋት የሚያስከትል ከሆነ ወይም የት/ቤቱን ወይም የክፍሉን ድባብ ወይም አሰራር በመሰረታዊነት የሚለውጥ ከሆነ ወይም ካልሆነ መወሰን።

f) ከ MCPS ውጪ የሚታወቁ ገንዘብ የማግኘት/ድጎማዎች የሚኖሩ ከሆነ ግምት ውስጥ ማስገባት፥ በሌሎች ት/ቤቶች ወይም ተቋማት ተመሳሳይ የማመቻቸት ሁኔታ ወይም የማሻሻያ ጥያቄዎች የተስተናገዱበት ተሞክሮ ካለ ግምት ውስጥ ማስገባት።

g) ውሳኔውን እና ድምዳሜ ላይ የተደረሰበትን ምክንያቶች ለጥያቄ አቅራቢው(ዋ) በፅሁፍ ማሳወቅ።

3. ለመፈፀም በሚቻልበት የጊዜ ማእቀፍ ውስጥ ውሳኔው መሰጠት አለበት።

D. ይግባኝ

1. ADA አስታባባሪ የሰጠ(ች)ው ውሳኔ ላይ አቤቱታ ለዋና ስራ አስኪያጅ/chief operating officer ሊቀርብ ይችላል።

2. በፅሁፍ አቤቱታ መቅረብ ያለበት ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ 10 ቀናት ውስጥ በጥያቄ አቅራቢው አካል ነው።

3. የምርመራ ሰነዶችን እና በጥያቄ አቅራቢው አካል በፅሁፍ የቀረቡ ክርክሮችን ለመገምገም የሰለጠነ የቅሬታ አጣሪ ሰራተኛ ይመደባል።

4. OCOO የቅሬታ አጣሪ ሰራተኛ የአቤቱታውን ውጤት እና ከውሳኔው ጀርባ ያለውን ምክንያት በመግለፅ የፅሁፍ ውሳኔ ይሰጣል።

5. OCOO የአቤቱታ አጣሪ ሰራተኛ ለጥያቄ አቅራቢ አካል በቦርድ ፖሊሲ BLB፣ አቤቱታዎች እና የአቤቱታ ብይን አሰራር ህጎችድንጋጌ መሠረት በስቴቱ ህግ ተሞርኩዞ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለቦርድ ይግባኝ ለማቅረብ ያላቸውን መብቶች ያሳውቃል።

E. OHRD በኩል አኮሞዴሽን ማመቻቸትን ጥያቄ መቀጠል ካስፈለገ ጠያቂ አካልን በቀጥታ ከመጠየቅ አያግደውም ወይም ወደ ሜሪላንድ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (MCCR) ይህንን ኢሜይል mccr.maryland.gov በመጠቀም ወይም ወደ በእኩልነት ሥራ የመቀጠር እድል ኮሚሽን (EEOC) በኩል በቀጥታ EEOC፣ ባልትሞር ዲስትሪክት ቢሮ አቤቱታ በቀጥታ ከማስገባት አይከለክልም፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission
Baltimore Field Office
GH Fallon Federal Building
31 Hopkins Plaza, Suite 1432
Baltimore, MD 21201
1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY)

G. የአጠቃላይ ካውንስሉ/የመማክርት ቢሮ (The Office of the General Counsel) ከ OHRD፣ የዲስትሪክት ስራ ሂደት ቢሮ፣ እና ከት/ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ኃላፊ ቢሮ ጋር በመወያየት፣ በዚህ ደንብ በተቀመጠው መሰረት ሀላፊነት ለተሰጣቸው ግለሰቦች በየወቅቱ የሙያ ትምህርት የማዘጋጀት ሀላፊነት አለባቸው።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Annotated Code of Maryland, State Government Article §20-601; Ann. Code, Education Article § 4-205; U.S. Constitution U.S.C., Amendment 14; Title VI of the Civil Rights Act of 1964, 42 U.S.C. § 2000d et seq; Title VII of the Civil Rights Act of 1964, as amended, 42 U.S.C. § 2000e et seq; Individuals with Disabilities Education Act (IDEA), 20 U.S.C. § 1400-1487; Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973, as amended, 29 U.S.C. § 794; Americans with Disabilities Act (ADA) 42 U.S.C. § 12131 et seq; Section 1981 of the Civil Rights Act of 1866, 42 U.S.C. § 1981

**የደንቡ ታሪክ፡-** አዲስ ደንብ ጁላይ 20፣ 1994፤ዲሴምበር 22፣ 2011 ተሻሻለ፤ ፌብሩዋሪ 1፣ 2023 ተሻሻለ።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን  ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፦ ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፦ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ  በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች  የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022